በደሴ ከተማ በወያኔ ፖሊሶች 7 ሰላማዊ ሰዎችን በጥይት መገደላቸው እና 14 መቁሰላቸው ተዘገበ

ከባህርዳር ህዝብ እንዲጨርስ በአያሌው ጎበዜ የቃል ትእዛዝ የመጣው ልዩ ሃይል ሰላማዊ ሰው ላይ አልተኩስም በማለት ምላሽ ሰጠ

የልዩ ሃይል አዛዥ  እጁን በካቴና ታስሮ  አዲስ አበባ ተወሰደ

በሰራዊቱ ውስጥ የተጀመረው የምንጠራ ዘመቻ ተጠናክሮ ቀጥሎዋል

በርካታ መኮንኖች ለቁም እስር እየተዳረጉ መሆኑ ተጋለጠ

የፌዴራል ፖሊስ አድማ በታች በጦር ካምፕ ውስጥ ግምገማ አደረጉ ብዙዎች ተባረሩ

አረመኔው የወያኔ ቡድን የተለመደውን በህዝብ ላይ ጭፍጨፋ የመፈጸም ተግባር በደሴ ከተማና አካባቢዋ ነዋሪዎች ላይ ዘመቻ መጀመሩን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለጸ

ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12 ሰዓት ተኩል ሲል በደሴ ከተማ 5 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው ሳር አምባ በተባለው ቦታ ላይ ህዝቡ የጸሎት ስነ ስርዓት ለማድረግ በተዘጋጀበት ወቅት የወያኔ የፖሊስ ሃይል ድንገተኛ የተኩስ እሩምታ በመክፈት 3 ሰዎችን ወዲያውኑ ሲገድል አስራ አራቱን ደግሞ ክፉኛ ማቁሰሉን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል

ከሶስት ዓመት በፊት የቤተክርስትያን ህንጻ ለመገንባት በከተማዋ አስተዳደርና በክልሉ መንግስት ጭምር የይዞታ ማረጋገጫ ካርታና የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው የደሴና አካባዋ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በተፈቀደላቸው መሰረት ስራ ለመጀመር ወደ ስፍራው አቅንተው ጸሎት በማድረግ ላይ እያሉ የፖሊስ ሃይሉ ድንገት የተኩስ እሩምታ በመክፈት ሁለት ለግላጋ ወጣቶችንና አንድ አዛውንት እናትን ገድሎ አስራ አራቱን ደግሞ ያቆሰለ ሲሆን ከቆሰሉት ሰዎች መካከል አራት ሰዎች ህይወታቸው በማለፉ የሙዋቾቹን ቁጥር ሰባት ሲያደርሰው ከስድሳ በላይ የሚሆኑ ሰዎችን ለእስራት መዳረጋቸውን  የደረሰን ዘገባ ጨምሮ አስረድቶዋል

የወያኔ ባለስልጣናት ራሳቸው ፈቃድ ሰጥተው ህዝበ ክርስትያን የማምለኪያውን ቦታ ግንባታ እንዲያከናውን የፈቀዱትን በመሻር ከሙስሊም ወገኖቹ ጋር ለማጋጨት ምንም ባልተፈጠረና ባልሆነ ወያኔ ሰራሽ ቅስቀሳ አድርገው ቦታው ውዝግብ ያለበት አስመስሎ በማቅረብ ግጭት ለመፍጠር ቢያስቡም ወንድማማችነቱ የበለጠበት የሙስሊሙ ህብረተሰብ በአርቆ አስተዋይነቱ የወያኔን ተልእኮ ሳይፈጽም በመቅረቱ የተበሳጩት የወያኔ ሆድ አደር ካድሬዎች የታጠቀ ሃይል በመላክ በክርስትና እምነት ተከታዮች ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋ እንዲካሄድ ማድረጋቸውን ዘገባው አብራርቶዋል

በተደጋጋሚ ግዜ ወደ ከተማዋ አስተዳደርና ወደ ክልሉ ባለስልጣናት በመሄድ ግንባታውን ለመጀመር አቤቱታ ሲያቀርቡ የቆዩት ህዝበ ክርስትያናት ምላሽ በማጣታቸው ቀድሞ በተሰጣቸው የይዞታ ማረጋጫ ካርታ መሰረት እና የግንባታ ፈቃድ ቀነ ቀጠሮ ቆርጠው ማክሰኞ ሰኔ 23 ቀን 20001 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12 ተኩል ላይ ከኮምቦልቻ ፣ ኩታበር ፣ ሃይቅ ፣ ደሴና ከአካባቢዋ ተሰባስቦ የመጣው ህዝብ በጸሎት ስራውን ለመጀመር እየተዘጋጀ ባለበት ወቅት « ጭር ሲል አንወድም » የሚሉት ነብሰ በላዎቹ የወያኔ ሆድ አደር ባለስልጣናት በማን አለብኝነት በሰላማዊው ህዝብ ላይ የጥይት ናዳ እንዲወርድበት ባዘዙት መሰረት ህዝበ ክርስትያን ለከፍተኛ ጉዳት የተዳረጉ መሆኑን ለማወቅ ተችሎዋል

የወያኔው አለቅላቂና የአማራው ህዝብ አንገት እንዲደፋ ሌት ተቀን የሚጥረው ሆድ አደሩ አያሌው ጎበዜ ከባህር ዳር ስድስት መኪና ፌጥኖ ደራሽ ጦር ልኮ ምእመናን እንዲመቱ ትእዛዝ የሰጠ ቢሆንም ሌሊቱን ተጉዞ ረቡእ እለት የደረሰው ፌጥኖ ደራሽ ኃይል ከህዝቡ ጋር ተነጋግሮ « እርምጃ አንወስድም ፤ አንድም ጥይት አናጮህም» በማለት ትእዛዙን ያመከነበት መሆኑን ለማወቅ ተችሎዋል

በዚህ የተበሳጨው አረመኔው አያሌው ጎበዜ ካድሬዎቹ በድምጽ ማጉያ በደሴ ከተማ ውስጥ እየተዘዋወሩ ችግር እንደተፈጠረ በማስመሰል እንዲለፍፉ ትእዛዝ መስጠቱን ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል

ሆድ እንጂ ማሰቢያ ህሊና ያልፈጠረባቸወ እነበረከት ስምኦን እራሳቸው ፈቃድ የሰጡበትን ቦታ መልሰው እንዳልተፈቀደ አድርገው ባመጡት ችግር ህዝቡን ወንጀለኛ በማስመሰል ጥረት ቢያደርጉም አልሳካ ሲላቸው የህዝቡን የእምነት ጥያቄ ከፖለቲካ ጋር በማገናኘት ከፍተኛ ቅስቀሳቸውን በተቆጣጠሩትና እንደፈለጋቸው በሚፈነጩበት ሬዲዮና ቴሌቭዥን ማሰራጨታቸው ታውቆዋል

ተወልደው ያደጉበትን ህዝብ ደም የመጠጣት አባዜያቸው አልለቅ ያላቸው አማራ ህዝብ ላይ እየወሰዱት ያለው እርምጃ አልጠቅምህ ስላላቸው አሁን ደግሞ በደሴ እና አካባቢዋ በሚገኙ የክርስትና እምነት ተከታዮች ላይ ግድያ ከመፈጸማቸውም በላይ እንዲጸድቅ በሚጠበቀው የሽብርተኝነት ህግ ህዝቡን ለመክሰስም ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ከዘገባው ለማወቅ ተችሎዋል

በከተማዋ ታዋቂ የሆኑ ግለሰቦች ጭምር ታፍሰው እስር ቤት የታጎሩ ሲሆን ቤታቸውም ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ድንገተኛ ፍተሻ ተደርጎበታል ያለው ዘገባ ወያኔ እራሱ ቦምብና የጦር መሳሪያ ደጃፋቸው ላይ እያስቀመጠ አገኘሁባቸው በማለት የህጻን ልጅ ቀልድ እየተጫወተ ከመሆኑም በላይ በሃሰት የተገኘው የጦር መሳሪያ የኔ ነው ብላችሁ ፈርሙ እየተባሉ ከፍተኛ ድብደባና ስቃይ እየተፈጸመባቸው የሚገኙ ዜጎች በእስር ቤት መኖራቸውን ጨምሮ አስረድቶዋል

ከባህርዳር ለሊቱን ሲገሰግስ ደሴ የገባው ልዩ ሃይል እርምጃ ካለመውሰዱም በላይ « እንደተባልነው ወንጀል ስትፈጽሙ አልተገኛችሁምና የታዘዝነውን አንፈጽምም ፤ ስለዚህ አትሸበሩ » በማለት ምእመናኑን እያረጋጉ ከመሆኑም በላይ « ድንገተኛ ሽብር ጣይ ቡድን በአካባቢው ሰፍሮዋል ፤ ተብለን ነበር የመጣነው ያየነው ግን ሌላ ነው አያሌው ጎበዜና በረከት ስምኦን ይህን ህዝብ ሊያስጨርሱ የሰጡንን ትእዛዝ ያሳፍራል እጅግ ያንገበግባል » በማለት የጦሩ አዛዥ ለህዝቡ መግለጹን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል

በዚሁ በደረሰን ዘገባ መሰረት የልዩ ሃይል አዛዥ የነበረው ኮማንደር የሻለቃ ማእረግ ያለው የአማራ ተወላጅ ሲሆን በአስቸኩዋይ ትእዛዝ «ተመለስ» ተብሎ በሌሎች ፖሊሶች ተይዞ ወደ ባህር ዳር መወሰዱ ታውቆዋል

የልዩ ሃይሉ አዛዥ ሻለቃ ወደ ባህር ዳር ትፈለጋለህ ተብሎ ይነገረው እንጂ ሃሙስ እለት ሰኔ 25 ቀን 2001 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ እጁን በካቴና ታስሮ መወሰዱን የገለጸው ዘገባ ተወርዋሪው ሃይል በቦታው እንደደረሰ በተኩስ እሩምታ ህዝቡን የመጨፍጨፍ ግዳጅ ተሰጥቶት ተግባራዊ ባለማድረጉ ለዚህ እስር እንደተዳረገ አስረድቶዋል

ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ቅዳሜ ስድስት ሰዓት ድረስ ህዘቡ በእልህ ወደ ቦታው በመሄድ የእምነት ተግባሩን እየፈጸመ ሲሆን በአካባቢው ተልኮ የነበረው ጦርም ያለአንዳች ችግር ከህዝቡ ጋር በመሆን በሰላም መቆየቱን ገልጾ በተጉዋዳኝ ግን የደሴ ታዋቂ ግለሰቦች ያስተባበራችሁት እናንተ ናችሁ ከጀርባችሁ የተቃዋሚ ድርጅቶች ድጋፍ አላችሁ እየተባለ ከየመኖሪያቸው ታድነው ወደ እስር እተጋዙ መሆኑን ዘገባው አጋልጦዋል

የወያኔ መሪዎች በበኩላቸው የራሳቸውን የእልቂት ድግስ አልደገስንም ብሎ ለመካድ እንዲያመቻቸው ግድያው የተፈጸመው የጦር መሳሪያ ከፖሊስ ሃይል ላይ ለመንጠቅ የሞከሩ ወገኖች በፈጸሙት ተግባር ነው በማለት እራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን አሳፋሪና አሳዛኝ የቅስቀሳ ሙከራ ቢያደርግም በወያኔ ድርጊት ሙስሊሙ ህብረተሰብ በእጅጉ እንደተቆጣ ከዘገባው ለመረዳት ተችሎዋል

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ የዛገራቱን ህዝብ ለማፈን ሲል በቅርቡ በጀመረው አዲስ ስልት ምክንያት የሽብርተኝነት ረቂቅ አውጥቶ ለምክር ቤቱ ያቀረበ በመሆኑ ህዝቡ ውስጥ ውስጡን በተቃውሞ እያጉረመረመ በመሆኑ የተደናገጡት እነበረከት ስምኦን የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስለወጥ ይረዳል በሚል ሌላ ከንቱ ቅስቀሳ እንዲደረግ ጥብቅ ትእዛዝ የፕሮፓጋንዳ ወፍጮዋቸውን ለሚፈጩላቸው ተላላኪ ካድሬዎቻው ማስተላፋቸውን ለማወቅ ተችሎዋል

የወያኔ የፕሮፓጋንዳ ቁንጮ በአሁኑ ሰሞን የሽብርተኛ ረቂቅ ህግ በማውጣት ህዝቡን አንገት ለማስደፋት እና ምንም የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት በአገሪቱ እንዳይኖር የሚያስችል ህግ በማውጣት ለተግባራዊነቱ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል

ይህ መሆኑ ደግሞ ህዝቡ በተቃውሞ በተለይም ኢህአዴግ አመጣሽ በሆነ መከራ ውስጥ ተዘፍቆ እንዲገኝ ስላደረገው ሁሉም ነገር ከአቅም በላይ ሲሆን በተለያየ መንገድ የተቃውሞ ድምጹን ለማሰማት የተገደደ መሆኑን ዘገባው ጠቁሞ ይህንን የህዝብ የልብ ትርታ ለማስለወጥ የቴሌቭዥንና የሬዲዮ ጋዜጠኞች ተዘዋውረው የዘገቡት በሚል ርእስ አንዳንድ ካድሬዎቻቸውን ቃለ ምልልስ በማድረግ የማዘናጋት እርምጃ እንዲወሰድ

የተሰጣቸውን መመሪያ ተቀብለው ለፕሮፓጋንዳ ስራቸው ሊሰማሩ መሆኑን አስረድቶዋል

ለአስራ ስምንት ዓመታት ያለ አንዳች ተቀናቃኝ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ላይ በደልና ግፍ ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ የቆዩት አባ ገብረ መድህን ከቅርብ ግዜ ወዲህ በስራቸው ካሉት የአዲስ አበባ ሃገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሳሙኤል ጋር በጀመሩት ሽኩቻ ከቤተክርስትያኒቱ ቀኖና ውጪ በህይወት ያለ ፓትርያሪክ እያላት በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጥምቀታቸው ጳጳስ ሆነው የቆዩ ቢሆንም አሁን ወንበራቸው መነቃነቅ ጀምሮዋል ብሎዋል ዘገባው

ከእምነት አባቶች በማይጠበቅ ሁኔታ እጅግ አስደንጋጭ እና አስጸያፊ የሆኑ ቃላትን በመሰንዘር  እርስ በእርስ እየተሞሽላለቁ ሲሆን ለአስራ ስምንት ዓመታት በህዝብ ላይ የሰሩት ግፍ በተለይ የወያኔን ጥይት ፈርተው በቤተክርስትያን ቅጥር ግቢ ተጠልለው የነበሩ ሰላማዊ ዜጎችን በግድ አስወጥተው እንዲገደሉና እንዲታሰሩ ማድረጋቸውን ብዙዎች በሃዘን የሚያስታውሱት መሆኑን ያመለከተው ዘገባ የግፍ ተግባራቸው በመብዛቱ የግፉአን እንባ ጠራጊ የሆነው ሃያሉ ፈጣሪ መልስ ሊሰጥ የመፈለጉ ፍንጭ የታየው በዚህ ሰሞን የአባ ገብረመድህንን ወንበር መነቃነቅና እንዳይወድቅ ደግፎ ለመያዝ የሚሰባበረው የወንዝ ልጅ ተብሎ በየጎጥ ተሰባብስቦ የነበረው ፍርፋሪ ለቃሚ ሆድ አደር ሲሰባበር ማየት በመቻሉ ነው ሲል ይኸው ዘገባ አስረድቶዋል

አባ ገብረመድህን ከአባ ሳሙኤል ያጋጫቸው ይህ ነው ብሎ ለመናገር ተጨማሪ የምርመራ መረጃዎችን ማጠናቀር ግድ የሚል ቢሆንም  በደህናው ግዜ ሁለቱ የሚያውቁትን ገመና ዛሬ በአደባባይ እንዲሰማና እንዲታወቅ ማድረጋቸው ሁለቱም እኩል መመሳሰላቸው፤ አንደኛው የመለስ ፤አንደኛው የአዜብ ነብስ አባት ወይም ሚስጢራዊ የጥቅም ተጋሪዎች መሆናቸውን በመተማመን ገመና አውጭ ሊሆኑ እንደቻሉ ግን ይነገራል

አባ ገብረመድህን በከተማ ፤ አባ ሳሙኤል በገጠር ሆነው ወያኔን ሲደግፉና ከምስኪኑ ህዝበ ክርስትያን ላይ የሚቀበሉትን የስለት ገንዘብ ለወያኔ መጠናከሪያ እንዲሆን ሲለግሱ እንደነበር የሁዋላ ታሪካቸው በጥቂቱ የተፈተሸበት ዘገባ ሁለቱም እስከ ዛሬ ድረስ አፍ ለአፍ ገጥመው ህዝበ ክርስትያኑን ሲያስገድሉና ሲያስጨፈጭፉ ቆይተው ድንገት በመሃላቸው በተከሰተ ግጭት የተነሳ አንዱ የአንዱን ገመና እያወጡ በሚሆነው ሁሉ ከመታዘብ ያልቦዘነው ህዝብ አሁንም በትዝብት እየተመለከታቸው መሆኑን አስረድቶዋል

በተለይ አባ ገብረመድህን ከወያኔ ሲደረግላቸው የነበረው ድጋፍ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በመቀነሱ የተነሳ ሲኖዶሱ ሥልጣናቸውን ነጥቆ ዋልጌ ፤ ስርዓተ ብልሹ መሆናቸውን አጋልጦ ለግዜው ሙሉ ስልጣናቸውን ነጥቆ የነበረ ቢሆንም በሰኔ ወር  መጀመሪያ ላይ ጣሊያን አገር ለስራ ጉዳይ በሚል ሽፋን ባደረጉት ጉዞ ችግሩ እየተስፋፋ መምጣቱን ለማወቅተችሎዋል

በአንድ ገበታ ብስል ከጥሬ ከውስኪ ጋር እያወራረደ በህዝበ ክርስትያኑ ላይ እያፌዘ በሁለቱም የጥቅም ፍላጎት ዙሪያ በተከሰተ ግጭት አንደኛው አንደኛውን ለማጥቃት የመንደርተኛ ወሬ በሚመስል ቁዋንቁዋ ሲሞሻለቁ መደመጣቸው ማንነታቸውን ፍንትው አድርጎ ያሳየ  ነው ያለው ዘገባ ከወትሮው በተለየ መልኩ የዚህ ሰሞኑ መወነጃጀልና መነቃቀፋቸው በርትቶ በመታየቱ አንገት አስደፊ መሆኑን ጨምሮ አስርቶዋል

አባ ጳውሎስ ለ18 ዓመታት የአስተዳደር ብልሹነት እንዲነግስ አድሎዋዊ አሰራር እንዲስፋፋ ሙስና እንዲፈጸም ያደረጉ መሆናቸውና በመንፈሳዊ አባትነት ብቻ እንዲቀመጡና የተቀረውን ስራ ጊዜያዊ ኮሚቴ እንዲረከበው በሚል ግንቦት 13 ቀን 2001 ዓ.ም. ሰባት ጳጳሳት ተመርጠው በሲኖዶሱ የተሾሙ ቢሆንም ገመናዬ ተጋለጠብኝ በማለት የጥቃት ዘመቻ በጳጳሳቱ ላይ የከፈቱ ሲሆን በተለይ አስተባባሪ ናቸው ብለው በጠረጠሩዋቸው አቡነ ሳሙኤል ላይ ጠንካራ እርምጃ እንዲወሰድ የእግዜሩ ቀርቶበት ለሚመኩበትና ለሚያምኑበት የፌዴራል ፖሊስ እና ደህንነት እንዲሁም ዋስ ጠበቃቸው መከበሪያዬ ፤ መኩሪያዬ ለሚሉት የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ ደብዳቤ መበተናቸው ታውቆዋል

በዚህም ምክንያት ሲኖዶሱ የሾማቸውን ሰባት ጳጳሳት በሙሉ ከኮሚቴ አባልነታቸው እንዲወጡ የሚያዝ ይህንንም ካልፈጸሙ ክህነት ማእረጋቸው እንደሚገፈፍ የሚገልጽ ጽሁፍ በሚስጢር ተዘጋጅቶ ለእየአንዳንዳቸው እንዲሰጥ ተደርጎ ነበር ሲል ዘገባው አጋልጦዋል

ደብዳቤው ከደረሳቸው ውስጥ ኮሚቴውን በሰብሳቢነት የሚመሩት አቡነ ሳሙኤል አንዱ ሲሆኑ እሳቸውም የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎችንና መምህራኖችን በመሰብሰብ በአባ ገብረመድህን እና በኮሚቴው መካከል  ስላለው ግጭት ሰፊ ማብራሪያ

መስጠታቸውንና የተቃውሞ መግለጫ ማውጣት አለባችሁ በማለት ድጋፍ ሲያሰባስቡ እንደነበር ዘገባው አስረድቶዋል

የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች በተሰጣቸው የአቡነ ሳሙኤል መመሪያ መሰረት ባለ ዘጠኝ ነጥብ መግለጫ ማውጣታቸውንና « የብልሹ አስተዳደርን መዋጋትና ሙስናን ያጋለጠ አባት ከስራው ሊታገድ አይችልም ፤ ድርጊቱን በጥብቅ እናወግዛለን » በማለት የተቃወሙ ሲሆን አቡነ ሳሙኤልም ልክ እንደ አባ ጳውሎስ ለፌዴራል ፖሊስና ደህንት ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮምሽን እና ለሌሎችም ተቁዋማት ትብብር እንዲደረግላቸው ጥሪ ማቅረባቸውንም ለማወቅ ተችሎዋል

በዚህ ውዝግብ ላይ ላይ እንዳሉ ከትናንት በስትያ የአቡነ ሳሙኤልን ከስልጣን ለማስነሳት ሲባል እስከ ዛሬ ድረስ በአንድ ጳጳስ ስትተዳደር የነበረችው የአዲስ አበባ ሃገረ ስብከት በአምስት ዞን ተከፋፍላ እየአንዳንዱ ዞን በጳጳሳት እንዲመራ የሚያዝ ደብዳቤ መበተናቸውን ታማኝ ውስጥ አዋቂዎች አጋልጠዋል

በአሁኑ ወቅት እንዲህ ያለ ሩጫ ላይ የሚገኙት አባ ገብረመድህን ከህዝበ ክርስትያኑ ላይ የዘረፉት ገንዘብ እንዳይጋለጥባቸውና በእምነት አባትነት ስም የወሰዱት አስጸያፊ ተግባራት እንዳይታወቅባቸው ሲሉ የሚያደርጉት ከንቱ የድብብቆሽ ሩጫ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አመልክቶዋል

ለወያኔ ስርዓት እድሜ ማራዘሚያ ሆነው በረሃ ለበረሃ ሲንከራተቱ የነበሩ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ሰበብ እየተፈለገላቸው ከስራ ገበታቸው ላይ እየተባረሩ ከመሆኑም በላይ በተጨማሪ ብዙዎች ለእስር እየተዳረጉ መሆኑን ከምእራብ እዝ የደረሰን ዘገባ አጋለጠ

ባለፈው ወር መጨረሻ ላይ የጀመረው ይኸው የሰራዊቱን አባሎች ግምገማ ለወያኔ ስርዓት በስልጣን ላይ መቆየት ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው መሆኑ ተነስቶ እውነትነቱ ተረጋግጦ ነበር

በዚሁ ግምገማ ወያኔ ማባረርና ማስወገድ ያለበትን በብሄር እየለየ የስም ዝርዝራቸውን ቀድሞ አዘጋጅቶ ነበርና የመልሶ ማጥቃት እርምጃ ወስዶ በሁለት መኮንኖች እና የበታች ሹማምንቶች ላይ የማባረር ውሳኔ ሰጥቶዋል

በሳሞራ የኑስ የሚመራው የምንጠራ ዘመቻ ሰሞኑን የሰሜን እዝ ተብሎ በሚጠራው የጦር ክፍል ዘልቆ በመግባት ግምገማ እየተደረገ ሲሆን በዚህ ግምገማ ላይ የበርካታ ለወያኔ ስርዓት መቆየት ጉልህ ድርሻ የነበራቸው እና የስርዓቱ ታማኝ ነን በማለት ህዝብን አንገት ሲያስደፉ የነበሩ መኮንኖቹ ጭምር ሰበብ ተለጥፎላቸው ከስራ የተባረሩ ፤ ገሚሶቹ ለቁም እስረኝነት እየተዳረጉ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል

በሜጀር ጄኔራል አብር ወልደማርያም የሚመራው ይኸው የደቡብ ምስራቅ እዝ ባለፈው ሳምንት ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም. በሃረር ከተማ ግምገማ የጀመረ ሲሆን በርካታ ለወያኔ ቡድን ሲያሸረግዱ፤ እወደድ ብለው ብዙ ሲያደርጉ የነበሩ መኮንኖች እና ባለሌላ ማእረግተኞች የሚሰጡት ጥቅም ያለቀ በመሆኑ እየተመነጠሩ እየተባረሩ ቢሆንም ያለምንም ርህራሄና አዘኔታ ከስራቸው በመባረራቸው ቤተሰቦቻቸው ለከፍተኛ ችግር እንደተጋለጡባቸውና እነሱም የመላው ኢትዮጵያውያንን ችግር ለመቅመስ እንደተገደዱ ለመገንዘብ ተችሎዋል

ወያኔን እንደጣኦት እያመለኩ ህዝቡ ቀና ብሎ እንዳይሄድና እንዳይናገር መሳሪያ ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩት እነዚህ መኮንኖች በወያኔ መሃከል በተፈጠረ ሽኩቻ ምክንያት እና እራሱን ግንቦት ሰባት ብሎ በሚጠራው ድርጅት ጋር ግንኙነት አላችሁ በሚል እየጠራረጉዋቸው ከመሆኑም በላይ ብዙ መኮንኖች እና ባለ ሌላ ማእረግተኞች ለእስር እየተዳረጉ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል

ሃገሪቱ ለድህነት ፤ ህዝቡ ለባርነት ለመዳረግ ሌት ተቀን ለሚራወጠው ወያኔ አጎብድደው ሲሰሩ የነበሩት እነዚህ የጦሩ አባላት ዛሬ ግዜው ደርሶ እነሱም የመባረሩን እጣ የወጣላቸው መሆኑና ከመሰናበታቸው በተጨማሪ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን አመለካከት ታራምዳላችሁ በሚል ለግዜው ለቁም እስር መዳረጋቸው በተመለከተበት ዘገባ በተለይ የዚህ ሰለባ የሆኑት የአማራው ተወላጆች መሆናቸውን ጨምሮ ገልጦዋል

ከቅርብ ግዜ ወዲህ እራሱን ግንቦት 7 ብሎ በሚጠራው ቡድንጋር በመሆን በመንግስት ተቋዋማት ላይ አደጋ ሊጥሉ ነበር ተብለው ከሽብርተኞች ጋር የስም ዝርዝራችሁ ተገኝቶዋል በሚል የፈጠራ ክስ ምክንያት ከ 30 ዓመትና ከ 20 ዓመት በላይ ከቆዩበት የሰራዊቱ ቤት ያለአንዳች ክፍያ እንዲበተኑ መደረጉን ዘገባው አመልክቶዋል

በአሁኑ ወቅት በሃረር ከተማ የምስራቅ እዝ እስር ቤት ውስጥ ቁጥራቸው ለግዜው ያልታወቀ የሰራዊቱ አባላት ታጉረው የሚገኙ ሲሆን በቀጣይም ይኸው ግምገማ በተባለው የመመንጠሪያ ስልት ብዙዎች እንደሚባረሩና እንደሚታሰሩ ዘገባው ገልጾዋል

መላው የሃገሪቱ ህዝብ በርሃብና በኑሮ ውድነት ሲሰቃይ ከአምባገነኑ ቡድን ጋር በመሆን የጀርባ አጥንትነታቸውን እያረጋገጡ እድሜውን ሲያራዝሙለት የነበሩት እነዚሁ የሰራዊቱ አባላት በድንገተኛው ግምገማ በሚል ፈሊጥ በወያኔ እንደሸንኮራ ተመጥጠው መተፋታቸው ለሌሎቹ ጥሩ ትምህርት ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች አሉ

በተመሳሳይ ወያኔ ባደረበት ውስጣዊ ፍርሃት የተነሳ በጦሩ ውስጥ የተጀመረው ግምገማና ምንጠራ ዘመቻ በሲቪል ተቋዋማት እና በፖሊስ ውስጥም በስፋት ቀጥሎ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሎዋል

ከአንድ ወር በፊት የተጀመረው የፌዴራል ፖሊስ ግምገማ አድማ በታች ከነበሩት የፖሊስ አባላትና ከአዲስ አበባ የፖሊስ አባላት በርካቶች ሰለባ መሆናቸውን ያመለከተው ዘገባ ለሶስት ዙር ተከታታይ በ15 ቀናት ልዩነት ሲደረግ የነበረው ግምገማ አብዛኞቹን እንዲባረሩና ውሳኔ እስከሚያገኙ ድረስ በልዩ ጥበቃ ስር ሆነው የሚሆነውን እንዲጠባበቁ መመሪያ መሰጠቱን ጨምሮ አስረድቶዋል

በጦላይ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ የተደረገው የፌዴራል ፖሊስ ግምገማ የታዘዛችሁትን በአግባቡ አልፈጸማችሁም ያልፈጸማችሁት ደግሞ ከህዝቡ ጋር እጅና ጉዋንት ስለሆናችሁ ነው በሚል በመወንጀላቸው ከፍተኛ ማእረግ ያላቸው የፖሊስ ባለስልጣናት ቁጣቸውን ገልጸው የነበረ ቢሆንም ወዲያውኑ ከስራ የመባረራቸው ውሳኔ ሊደርሳቸው ችሎዋል

ሌላ የመብት ጥያቄም እንዳያነሱ ጥፋታቸው በፍርድ ቤት በሚመሰረት ክስ የሚታይ ይሆናል የሚል ቅድመ ማስፈራሪያ የደረሰባቸው መሆኑንም ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል

በዘገባው መሰረት አምስት የፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ባለስልጣን የነበሩ ዛሬ በእስር ላይ ሆነው ምርመራ እየተደረገባቸው መሆኑን በፌዴራል ማረሚያ ቤት በሚባለው የወያኔ ማጎሪያ ካምፕ የጥበቃ ፖሊስ መምሪያ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ ከፍተኛ አመራሮቹ ግምገማ እንደተቀመጡ እንዲሁም ባለፈው ረቡእ በደብረዘይት ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ  ግቢ ውስጥ ለእረፍት እንኩዋን እንዳይወጡ የተከለከሉ እና ጥበቃ ተመድቦባቸው ምሽትና ቀን እርስ በእርስ እየተገማገሙ መሆኑን ከወያኔው የመከላከያ ምንጮች የደረሰን ዘገባ አረጋግጦዋል